**''ያለኝ ድጋፍ ስለመቀነሱ ማስረጃ የለም''**

ዶር ዐብይ አህመድ

በአዲስ ተስፋ

addiste@gmail.com

መቼም ፖለቲከኛ ሲባል ውሸትና ክህደት ምሱ ይመስል በሚሊዮኖች ፊት የቅጥፈት ዲስኩር ማድረጉ አዲስ ሊሆን አይችልም። ዶክተር አብይ በተለያዩ ውጥረቶች ውስጥ እንዳሉ የሚታወቅ ቢሆንም ደረቅ ክህደት ይክዳሉ ተብሎ ግን አይጠበቅም። በኦገስት አንድ ሁለት ሺህ አስራዘጠኝ ዓም በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በሰጡት መግለጫ ካነሷቸው በርካታ ጉዳዮች አንዱ ስለራሳቸው ድጋፍ መቀነስ አለመቀነስ የሰጡት ማብራሪያ ከልብ የሚያስፈግግ ነበር። የእኔ ድጋፍ እንደቀነሰ የሚያሳይ ማስረጃ የለም ብለዋል። በሌላ አባባል ያገኘሁት የህዝብ ድጋፍ መቶ በመቶ እንዳለ ነው ማለታቸው ይሆን? ምናልባት እኝህ ሰው ከመረጃ ርቀው ከሆነ ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው በማለት ስለ እርስዎ እንዲህ እየተባለ ነው ተብሎ መረጃው እንዲደርሳቸው ማድረግ ይቻል ነበር። ነገር ግን አካሄዳቸው አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም እንዲሉ ነውና ቅጥፈት ወይም ክህደት ካልሆነ በቀር ቢያንስ የአለም ዓቀፍ ሚዲያዎች እርሳቸውን በተመለከተ እያወጡ ያሉትን ዘገባ ብቻ በማገናዘብ አወ በተለያዩ ምክንያቶች ድጋፌ ቀንሷል ቢሉ ኖሮ ከበሬታቸው በጨመረ ነበር።

እንደ እውነቱ ከሆነ የድጋፋቸው መቀነስ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያችንን ታይቶና ተሰምቶ በማያቅ የግጭት ማእበል እያስገቧት እንደሆኑ በድፍረት የሚነግራቸው ጠፍቷል። ዛሬም እኔ እስረኞችን ፈትቻለሁ ፣ የሚድያ ነጻነትን አምጥቻለሁና ሌላም ሌላም አዎንታዊ ገጽታቸውን በመናገር ብቻ መልካም መሪ መሆናቸውን ሊነግሩን ይሞክራሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ ድጋፋቸውን ያሳጧቸውና በመላው ኢትዮጵያዊ ዘንድ በጥርጣሬ እንዲታዩ ያደረጓቸው የራሳቸው ወገኖች ጽንፈኝነትና ህገ ወጥነት መሆኑን ለማዎቅ የፈለጉ አይመስልም። ራሱን የፖለቲካ ሳይንቲስት ብሎ የሚጠራው ጃዋር መሃመድ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ግልጽ የሆነ የጥላቻ ንግግር ብቻ ሳይሆን ጦርነት እያወጀ እየሰሙና እያዩ ምንም አይነት ህጋዊ ርምጃ እንዲዎሰድበት አልፈቀዱም። ጃዋር ግልጽ በሆነ መንገድ በትግራይ ህዝብ ላይ፣ በአማራ ህዝብ ላይ፣ በሶማሊያና በደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ በሚመራው ሚዲያ ግልጽ የሆነ ጦርነት አውጆ በርካታ ሰዎች እንዲሞቱና ንብረት እንዲዎድም አድርጓል። ታሪክ ሂደቱን እየመዘገበ ይገኛል። ከህውሃትና ጌታቸው አሰፋ ጋር በተያያዘ በትግራይ ላይ በተደጋጋሚ የጥላቻ ዘመቻ ሲያካሂድ ነበር። የሌባ መሸሸጊያ በማለትም ህዝቡን በብዙ ሲያሸማቅቅ ነበር።

በርካታ ማስረጃዎችም አሉ። የዐማራን ህዝብ በተመለከተ ደግሞ በቤንሻንጉል በትግራይ በኦሮምያና በአፋር አጎራባች ስፍራዎች በተደራጀ መልኩ ስፖንሰር እየተደረጉ የተነሱ ግጭቶችን ምክንያት በማድረግ በሚመራው ሚዲያ እስኪሰለች ድረስ ለአማራ ያለውን ጥላቻ በሚፈልገው መንገድ ሙሁራን የሚላቸውን በመጋበዝ ጭምር የሚፈልገውን ፕሮፓጋንዳ ከመስራት በተጨማሪ ግልጽ የሆነ ጦርነት አውጇል። አያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ እንጂ የካርታህ ፊልም ተቃጥሏል ያለው የአማራ ህዝብ ግን በየትኛውም አቅጣጫ ማንም ሳያግዘውና የቆመለት አካል ሳይኖር ብልሃት በተሞላበት ሁኔታ ጥላቻውንም የጦርነት እወጃውንም ተቋቁሞታል። አዴፓ ወይም አብን ለዚህ ምንም የሰሩት ተጨባጭ እንቅስቃሴ አልነበረም።

የዐማራ ህዝብ ግን በጊዜያዊ ደባዎችም ሆነ በቋሚ ጠላቶቹ ላይ ታጋሽ ነው። ጃዋርና መሰሎቹ ይህንን ሁሉ ሲያደርጉ ዶክተር አብይ ደጋፊ ከመምሰል ውጪ አንዲትም የወሰዷት ርምጃ አልነበረችም። **ታዲያ ቢያንስ እንደዛ በገፍ ወጥቶ የደገፋቸው የዐማራ ህዝብ ቢያንስ ዝም ማለቱ እየተገደለና እየተወገዘ ድጋፉን ቀጥሏል ብለው አስበው ከሆነ ምናልባትም ኢትዮጵያን ስለታላቅነቷ ያወራሉ እንጂ አያውቋትም ማለት ነው።**

የሶማሊያ የጎሳ መሪዎችና ሽማግሌዎች እንዲሁም አሁን በምክትል ርዕሰ መስተዳድርነት የሚያገልግሉት አቶ ሙስጠፌ  ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ በኦሮሞና ሶማሌ መካከል የተነሳውን ግጭት ባይፈቱት ኖሮ የኦሮሞ አባገዳዎችና ሽማግሌዎችም  የጽንፈኞችን አካሄድ በሽምግልና ባያከሽፉት ኖሮ በሁለቱ ነገዶች መካከል ያለው ግጭት ፈጽሞ የማያባራ በሆነ ነበር። **ታዲያ ይህ ቤቱና ንብረቱ የተቃጠለበት፣ ከሚኖርበት ቀየው የተባረረው ፣ የተገደለውና ንብረቱ የወደመበት ምስራቃዊ ፈላጭ ቆራጭ የሆነው አብዲ ኢሌን እስር ቤት ስላስገቡለት ብቻ ዶክተር አብይን እየደገፈ የሚቀጥል መስሏቸው ከሆነ ዶክተሩ የኢትዮጵያውያንን ስነልቦና ገና አልተረዱም ማለት ነው።**

ስለ ጌድዮና ጉጂ ግጭትስ ምን እናውራ ? ጃዋር በሰሜን ሸዋ በኬሚሴና በምስራቅ ሸዋ አካባቢ የተነሱትን የማንነት ጥያቄዎች የዐማራ መስፋፋት እያለ ጥላሸት ለማልበስ ሲሞክር የራሱ ጋሻዣግሬዎች ገዲዮንን ለመጠቅለል የሚያደርጉትን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ማፈናቀል ግን አንዲት ቃል ለመተንፈስ ፈቃደኛ አልነበረም። ይልቁንም ለዚህ ቅድመ ሁኔታ ያመቾ ዘንድ **ሲዳማዎች ያነሱትን የክልል** እንሁን ጥያቄ መግፋት የስትራቴጂው አካል ስለነበረ **በሃይልም ቢሆን ሲዳማ ክልል መሆን አለባት** ብሎ በአደባባይ ሲያውጅ የዶክተር አብይ መንግስት አንዲትም ቃል አልተነፈሰም። ታዲያ ትናንት በነቂስ ወጥቶ የደገፋቸው የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬም መቶ በመቶ እንደሚደግፋቸው በኩራት ሲናገሩ ክህደት ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል?

**በትግራይና በአማራ ክልሎች መካከል አንዴ ሞቅ አንዴ ቀዝቀዝ እያለ የቀጠለው ግጭት ሰርግና ምላሽ የሆነላቸው ዶክተር አብይ ግጭቱ መፍትሄ እንዲያገኝ በምንም ተዓምር እንደማይፈልጉ በተጨባጭ አሳይተዋል።** በፖለቲካ ብስለትም ይሁን የህዝብ ስሜትን በማነሳሳት ለአላማዋ ግብ መምታት የምትጠቀመው ህወሃት ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታውን በማስበለጥ ከአዴፓ ጋር እሰጣ ገባ የገጠመች ቢመስልም፣ አዲስ አበባ የራሴ ነች በማለት የመግለጫ መዓት በኦዲፒ በኩል ሲስተጋባ ዝምታን መምረጧና የአዴፓን አቋም ላለመደገፍ በሚመስል መልኩ ዝም ማለቷ ፣ በቀለ ገርባና ህዝቄል ጋቢሳን የመሳሰሉት ጎሰኝነታቸው ጫፍ የወጣባቸው ግለሰቦችን በመቀሌ ዩኒቨርሲቲና በትግራይ ክልል ጽሁፎች እንዲያቀርቡ መጋበዟና ተገፍታ የተወረወረችበትን የማእከላዊ ስልጣን ለማስመለስ በምታደርገው ትግል ግባቶችን ለመሰብሰብ መሆኑን ያልተረዱ ግብዞች **ለኦሮሞ ጎጠኞች ህወሃት የከፋ ንቀት እንዳላት ቢገባቸውም ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት ሌላ ቁማር ሲቆምሩ እያየናቸው ነው**። ህወሃት ፊቷን ወደ አዴፓና አንድነት ፈላጊው ኢትዮጵያዊ የምታዞርበት ጊዜው ገና ቢመስልም አንዳች እየተሰራ ያለ የህቡእ እንቅስቃሴ እንዳለ ግን ኦነጋዊያንና ጆሃራዊያን ሊረዱት የረፈደባቸው ይመስላል። ዶክተር ደብረጽዮን በትግራይ አለማቀፋዊ ኮንፈረንስ ላይ ባደረጉት ንግግር እኛ **የአማራን ህዝብ ትምክህተኛ አላልንም። እንዲያዉም ጦርነቱ እንዲቀር የረዳን የዐማራ ህዝብ ነው** በማለት ረዘም ያለ ዲስኩር አሰምተዋል። ይህ አባባላቸው ወቅታዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ደጋግመው የተናገሩትም ነው።የኢትዮጵያን ፖለቲካ ዳይናሚክስ ለመቀየር ካስፈለገ ከየትኛውም ድርጅት በተሻለ ህወሃትና አዴፓ የተሻለ ልምድ አላቸው። **የቀደመውን የህወሃት ክፍፍልና የዶክተር አብይን ወደ ስልጣን መምጣት ብቻ በመመልከት ስለዚህ ጉዳይ ሰፋ ያለ ትንታኔ መስጠት ይቻላል። ህወሃትም ለህልውናዋ የመጨረሻ የመሰለውን ክፍፍሏን ያስተናገደችበትና ድርጅት ሆና እንደገና የቀጠለችበት መንገድ ፣ አዴፓም ህጋዊና ፖለቲካዊ ጠቅላይ ሚኒስቴር የመሆን መብቱን በመተው ስልጣንን ወደ ዶክተር አብይ ያስተላለፈበት መንገድ ሁለቱ ፓርቲዎች ግንባር የመፍጠር አጋጣሚ  ካገኙ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዳይናሚክስ ፈጽሞ እንደሚቀየር ምንም ጥርጥር የለውም። ዶክተር አብይ እርሳቸው መፈንቅለ መንግስት ብለው የጠሩት የዐማራ ክልል ባለስልጣናትና የፌደራል መንግስቱ ጀነራሎች ግድያ ምንም እንኳ የተቀነባበረ እንደሆነ በርካታ ምሁራንና የፖለቲካ ተንታኞች ቢገልጹም በከፍተኛ ሁኔታ የዶክተሩን ድጋፍ ያሳጣ ክስተት ነበር።** ተጠቃሚው ህወሃት፣ አዴፓ ወይስ አሁን የአገሪቱን ስልጣን እንደ ሬሽን የተከፋፈለው የዶክተር አብይ ፓርቲ?

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የዐማራን ህዝብና ባለስልጣናት በማጽናናትና በመደገፍ የክልሉን ሰላም ማረጋጋት የሚገባው የዶክተር አብይ መንግስት የዐማራን ልሂቃን፣ ፖለቲካኞችና ባለሃብቶች በገፍ በማሰር በማሳደድና በማስፈራራት እውነት ተዳፍና እንድትቀር በመትጋት ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያ ሲሉ ከፍተኛ ድጋፉን ያሳያቸው በብዙ አስር ሚሊየኖች የሚቆጠረው ኢትዮጵያን በመገንበት ቀደምት የሆነው የዐማራ ህዝብም የዶክተር አብይ ጭምብል በመገለጡና ማንነታቸውን በግልጽ በመመልከቱ የሰጣቸውን ድጋፍ ሲቀማቸው በብዙ ትእግስት በመታጀብ ነው። በመላው ኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባና በአማራ ክልል ዜጎች የአብን አባላትና ደጋፊዎች ሆናችሁ ተብለው ወደ እስር ቤት ታጋዙ። የአዲስ አበባ ባላደራ ምክርቤት አመራሮችና ደጋፊዎችም እየታደኑ በመታሰር ላይ ይገኛሉ። ህወሃት ምንም እንኳ በ1968 ዓም በጻፈችው ማኒፈስቶዋ የዐማራን ህዝብ እንደጠላት የፈረጀች ቢሆንም የአንድነትና የህብረት ደጋፊና የጎሰኝነት ተቃዋሚ የመሰሏትን ሁሉ ትምክህተኛና የድሮ ስርዓት ናፋቂ በማለት በገፍ ታስርና ታሳድድ ነበር። ኦሮሞውን ጠባብ፣ አማራውን ትምክህተኛ ሌላውን ኢትዮጵያዊ ደግሞ የቀድሞ ስርዓት ናፋቂ በማለት ሁሉንም የራሷን ስርዓት አስጊ የመሰሏትን ሁሉ በጅምላ ታሰቃይ ነበር። የዶክተር አብይ መንግስት **ደግሞ ዐማራን ብቻ በመምረጥ** የመንግስት ግልበጣ አድርጋችኋል በማለት ከያለበት በመሰብሰብ በእስራትና በማሸማቀቅ ያመነውን ህዝብ ክዷል። ይህ ለህወሃት ሰርግና ምላሽ ነው። **ዶክተሩም በዚህ መጠን የወረደውን ተቀባይነት ማጣት በጥናት አልተደገፈም ብለው አሁንም ቅቡል ነኝ ይሉናል።**

በአንድ ወቅት ራሳቸው ዶክተር አብይ የራሳቸውን ነገድ አባላት ሰብስበው ፈረንጆቹ በእኛ የአመራር ብቃት ጥያቄ አላቸው፤ እናንተ አገር መምራት አትችሉም በመንደር የተገደባችሁ ናችሁ ፤ ጎጠኛ ናችሁ ይሉናል። አስተሳሰባችንን ታላቅ ማድረግና ኢትዮጵያን መምራት እንደምንችል ማሳየት አለብን በማለት ተራማጅ አስተሳሰብ እናዳላቸው ለማብራራት ሞክረው ነበር። ነገር ግን እርሳቸው ራሳቸው አድሎ በተሞላበት መንገድ ዐማራን በማሳደድ፣ ህገመንግስት ይሻሻልልኝ ያለውን ዜጋ በማሰር ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ መፈንቅለ መንግስት አካሄዱብኝ በማለት በእርግጥም አገር የመምራት ብቃትና መልካም አስተዳደን ማስፈን እንደማይችሉ እያሳዩን ይሆን?

የዐማራ ህዝብ እንዲሁም አጠቃላዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ወሰን በሌለው ትእግስቱይታረሙ ይሆንል ፣ ከጽንፈኛ የነገዶቻቸው ፖለቲከኞች ከፍተኛ ተጽዕኖ አለባቸው በመሆኑም ጊዜ ያስፈልጋቸዋል በማለት ስ ህተቶቻቸውን ሁሉ እያየ እንዳላየ ቢሆንም ስልጣኔን አደላድያለሁ፣ በርካታ ወሳኝ በታዎችንም በምፈልጋቸው ሰዎች ሞልቻለሁ ያሉ በሚመስል ሁኔታ ዐማራውን ወደ ማጥቃት ተሸጋገሩ። በተግባራቸውም የመናገር ነጻነትም ይሁን መደራጀት አበቃ እያሉን ይገኛሉ። በትናንትናው ንግ ግራቸው ምርጫ ቢደርግ እንኳ መስረቅ ልማዱ የሆነው ፓርቲያቸው ሊጸዳ እንደማይችል በአደባባይ ሲነግሩን ቀደም ብለው እነጅዋር በምርጫም ይሁን በሌላ መንገድ የምንፈልገውን እናደርጋለን ብለው የነገሩንን እቅድ ማጽናታቸው ነበር። ዶክተሩ ያልተረዱትና ያልተገነዘቡት ለራሳቸው ድጋፍ መቀነስ ብቻ ሳይሆን መቀበሪያቸውን ጉድጓድ እየቆፈሩ መሆናቸውን ነው። እምቢ ለነጻነቴ በማለት ወደፊት እንዲመጡ ምክንት ያት የሆናቸውን አንድነትና ኢትዮጵያን ፈላጊውን ህዝብ መካድ ብቻ ሳይሆን ማሳደድ ማሰርና መሸማቀቅ መጀመራቸው ለመክፈል የከበደና እዳና መራራ ጽዋ እንደሚያስጎነጫቸው ምንም ጥያቄ የለውም። ህወሃት ለሶስት አስርት አመታት የጫነችበትን ቀንበር ሰብሮ ነጻነቱን ያወጀ መሆኑን መዘንጋት ፣ በዐለም ዓቀፍ ደረጃም የህወሃት ኢህዐዴግን ተቀባይነት ባዶ ያደረገ፣ ባለስልጣናት ሁሉ በህግ እንዲጠየቁ እንቅስቃሴ በማድረግ ወደ መጨረሻ ውጤት ያመጣው ዲያስፖራ የዶክተሩን እጅግ አሳሳቢ ፖለቲካዊ ስብእና ዝም ብሎ የሚመለከት መስሏቸው ከሆነ መሰረታዊ የሆነ ስህተት ላይ ወድቀዋል ማለት ይቻላል። ዶክተር አብይ ውድቀታቸው የጀመረው የሰለቸንን የሴራ ፖለቲካ እንደገና ነፍስ ሲዘሩበት ነው።

ስለ ድጋፋቸው መቀዛቀዝ በመረጃ የተደገፈ አይደለም ላሉት መልስ ለመስጠት ሳይሆን መረጃ ማለት ምን ማለት እንደሆነ መንገር ከቻሉ የስድስት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ግድያ ሰዓታት ባልሞላ ጊዜ መፈንቅለ መንግስት ነው ብለው መግለጫ የሰጡበትን መረጃዎትን ቢያሳዩን ለእርስዎ አምነት በኖረን ነበር። ለመሆኑ በምን ፍጥነት መረጃ ደርሶዎት ይሆን አማራ ክልል የመፈንቅለ መንግስቱን ለማክሸፍ ባለስልጣናት ገዳዮችን ተኩሰው እንዲገድሉ ፈደራል ፖሊስና ወታደሮቹን የላኩት? ግድያው በ11ሰዓት አካባቢ ተካሄደ፣ ፈደራል ፖሊስና መከላከያም በ 11 ስዓት ባህርዳር ምክርቤት ተገኝቶ ተታኮሰ። ክልልነትን እናውጃለን ያለው የሲዳማ ክልል ኤጀቶ ከወራት በፊት

አስጠንቅቆ ሃምሌ 11 ግድያና ዘረፋ ሲፈጸም ያልደረሰው መከላከያና ፌደራል ፖሊስ በአይን ቅጽበት ባህዳር ምክርቤት ተታኩሶ መፈንቅለ መንግስቱን አክሽፏልአሉን።በቅጽፈተ አይን አማራን የወረረው መከላከያና ፈደራል ፖሊስ ምእራብ ኦሮሚያ ከ18 በላይ ባንኮች ሲዘረፉ ፣ ዜጎች በገፍ ሲገድሉና ሲሳደዱ ፣የጌድዮ ተፈናቃዮች በታጣቂዎች ሲገደሉና ሲፈናቀሉ በቤንሻንጉል በርካታ ሰዎች ሲያልቁና ሲፈናቀሉ ክልሎች ከአቅሜ በላይ ነው ብለው አላመለከቱም ፈደራልና መከላከያ እንዲገባም አልፈቀዱም በማለት ረዥም ጊዜ ወስዶበታል። ታዲያ እንደዚህ አይነት አይን ያወጣ አድልዎ እያሳዩ ድጋፍዎት ለመቀነሱ ማስረጃ አልቀረበም ማለት ከእርስዎ የሚጠበቅ ነውን?

ኦገስት 2019